# የኢየሩሳሌም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን
# የሕንጻ ፕሮጀክት

**አጭር ሪፖርት፤ 2016-08-28**

# ጥቂት መረጃዎች

- ኢጥቢያ ቤተክርስቲያናችን ከ1999/2000 ዓ.ም. ጀምሮ የራሷ የሆነ ህንጻ እንዲኖራት ላለፉት 16 ዓመታት ስታልም/ስታቅድና/ስትዘጋጅ ቆይታለች
- **<u>"የሕንጻ ፕሮጀክት"</u>** የቤተክርስቲያን መሪዎችን ሕንጻን በማፈላለግ ለማገዝ የተቀመጠ ጊዜያዊ ፕሮጀክት ነው
- ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያካሂድ ቆይቷል

# የፕሮጀክቱ አባላት

- ወሰን ተሾመ
- ሙሴ ኃይሉ
- አለምተስፋ ላቀው
- ዮሐንስ ዓሥራት

# የፕሮጀክቱ ዓላማ

- ”ለአጥቢያ ቤተክርሲቲያናችን የሚሆንን እኛ ባለቤት የሆንንበትን ስፍራ ለማፈላለግ ከቤተክርስቲያን መሪዎችን ጋር በቅርበት እየሰሩ እርምጃዎችን ለመውሰድ መርዳት።”

# ከዚህ ቀደም የተደረጉ እንቅስቃሴዎች...

- በ2005 ዓ.ም. ፍሩኤንገን የሚገኝን አንድ ሕንጻ
- በ2009 ዓ.ም. አሁን ያለንበትን ሎካል **በኪራይ** ማግኘት ተቻለ
- በ2009ና 2010 የአባልነት ክፍያ (”ሜድሌምስ አቭዩፍት”)
- በ2010 ዓ.ም. ፎቶግራፍ ተነስተን "የአባልነት ምስክርነት ወረቀት”
- በ2010/2011 ገንዘብ ረዘም ላለ ጊዜ በማስቀመጥ (>310000)
- ከ2012 የሴትራ ቤተክርስቲያን (Sätra kyrkan)
- በ2012 ለፍተትስ ሺርካ (Löftets kyrka)
- በ2015 በማሪያቶርየት (St Paulkyrkan på Mariatorget)
- በ2016 ጃንዋሪ ከ3000 ካሬ በላይ ፍሪቲድስ ጎርድን ኡፕሳላ

# አሁን ያለንበት ሁኔታ

- በሜይ 2016 አሁን ካለንበት ሎካል ባለቤቶች ተወካይ ጋር
- ከዚህ የተነሳ በአሁኑ ጊዜ በአዲስ መልኩ እንቅስቃሴ ለማድረግ እየተነሳሳን እንገኛለን

# ከእስራኤላውያን ወደተስፋይቱ ምድር ከመግባታቸው የሚመሳሰልበት ነገር...

1) ይህ ስራ እግዚአብሔርን መታመንን ይጠይቃል

2) የኛ "የዔናቅ ልጆች"

- እጦቶቻችንና ዛሬ ያለን የቦታ ችግር
- አለማመን
- እግዚአብሔር ትናንት ያደረገውን ተአምራት መርሳት
- ከአቅማችን በላይ የሚመስሉ ችግሮች ("የተዘጋ በር" "እውቀት ልምድ ኮንታክት የለንም ብለን ማስብ")
- የማይታየውን ትተን የሚታየውን ስንመለከት

# ዘዳግም ፤:19-36

- 26 "በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ ዓመፃችሁ እንጂ **ወደ እርስዋ መውጣትን እንቢ አላችሁ**.....
- 32-34ዳሩ ግን ለሰፈራችሁ የሚገባውን ስፍራ እንዲፈልግላችሁ፥ ትሄዱበት ዘንድ የሚገባውንም መንገድ እንዲያሳያችሁ ሌሊት በእሳት፥ ቀን በደመና በፊታችሁ በመንገድ ሲሄድ የነበረውን **አምላካችሁን እግዚአብሔርን በዚህ ነገር አላመናችሁም።** እግዚአብሔርም የቃላችሁን ድምፅ ሰምቶ ተቆጣ።ለአባቶቻችሁ እሰጣት ዘንድ የማልሁላቸውን መልካሚቱን ምድር ከእነዚህ ሰዎች ከዚህ ክፉ ትውልድ ማንም አያይም፥
- 36፤ **ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብ በቀር እርሱ ግን ያያታል፤** **እግዚአብሔርን ፈጽሞ ተከትሎአልና** የረገጣትን ምድር ለእርሱ ለልጆቹም እሰጣለሁ ብሎ ማለ።"

# ዘዳግም 8:1-

2፤ አምላክህ እግዚአብሔር ይፈትንህ ዘንድ፥
በልብህም ያለውን ትእዛዙን ትጠብቅ ወይም
አትጠብቅ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ፥ ሊያስጨንቅህ
በእነዚህ በአርባ ዓመታት በምድረ በዳ የመራህን
መንገድ ሁሉ አስብ። 3፤ ሰውም ከእግዚአብሔር አፍ
በሚወጣ ነገር ሁሉ በሕይወት እንዲኖር እንጂ ሰው
በእንጀራ ብቻ በሕይወት እንዳይኖር ያስታውቅህ
ዘንድ አስጨነቀህ፥ አስራበህም፥ አንተም
ያላወቅኸውን አባቶችህም ያላወቁትን መና አበላህ።

# ዘዳግም 9:19-36

- 1 እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ከአንተ የበለጡትንና የበረቱትን አሕዛብ፥ እስከ ሰማይም ድረስ የተመሸጉትን ታላላቆች ከተሞች ለመውረስ ትገቡ ዘንድ ዛሬ ዮርዳኖስን ትሻገረዋለህ።
2 አንተም የምታውቃቸው ስለ እርሱም፦ በዔናቅ ልጆች ፊት መቆም ማን ይችላል? ሲባል የሰማኸው ታላቁና ረጅሙ ሕዝብ የዔናቅ ልጆች ናቸው።
**3 አምላክህም እግዚአብሔር እንደሚበላ እሳት ሆኖ በፊትህ እንዲያልፍ ዛሬ እወቅ፤ እርሱ ያጠፋቸዋል፥ በፊትህም ያዋርዳቸዋል፤ እግዚአብሔርም እንደ ነገረህ አንተ ታሳድዳቸዋለህ፥ ፈጥነህም ታጠፋቸዋለህ።**

# ዘዳግም 10:16-21

16፤17፤ እንግዲህ አምላካችሁ እግዚአብሔር የአማልክት
አምላክ የጌቶችም ጌታ፥ ታላቅ አምላክ ኃያልም
የሚያስፈራም፥ በፍርድ የማያደላ፥ መማለጃም የማይቀበል
ነውና እናንተ የልባችሁን ሸለፈት ግረዙ፥ ከእንግዲህ ወዲህም አንገተ
ደንዳና አትሁኑ።18፤ ለድሃ አደጉና ለመበለቲቱ ይፈርዳል፥ መብልና ልብስም ይሰጠው ዘንድ
ስደተኛውን ይወድዳል።19፤ እናንተ በግብፅ አገር ስደተኞች ነበራችሁና ስለዚህ ስደተኛውን
ውደዱ።20፤ አምላክህን እግዚአብሔርን ፍራ፥ እርሱንም አምልክ፤ ከእርሱም ተጣበቅ፥ በስሙም
ማል።21፤ ዓይኖችህ ያዩትን እነዚህን ታላላቆች የሚያስፈሩትንም
ነገሮች ያደረገልህ እርሱ ክብርህ ነው፥ እርሱም
አምላክህ ነው።22፤ አባቶችህ ሰባ ነፍስ ሆነው ወደ ግብፅ ወረዱ፤ አሁንም
አምላክህ እግዚአብሔር ብዛትህን እንደ ሰማይ ከዋክብት አደረገ።

# ዘዳግም 20:1-4

1፤ ጠላቶችህን ለመውጋት በወጣህ ጊዜ፥ ፈረሶችንና ሰረገሎችን ሕዝቡንም **ከአንተ ይልቅ በዝተው ባየህ ጊዜ**፥ **ከግብፅ አገር ያወጣህ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና አትፍራቸው።**2፤ ወደ ሰልፍም በቀረባችሁ ጊዜ ካህኑ ይቅረብ ለሕዝቡም እንዲህ ብሎ ይንገራቸው።3፤

**እስራኤል ሆይ፥ ስሙ፤ ዛሬ ጠላቶቻችሁን ለመውጋት ትቀርባላችሁ፤ ልባችሁ አይታወክ፥ አትፍሩ፥ አትንቀጥቀጡ፥ በፊታቸውም አትደንግጡ፤4፤ ከእናንተ ጋር የሚሄድ፥ ያድናችሁም ዘንድ ጠላቶቻችሁን ስለ እናንተ የሚወጋ አምላካችሁ እግዚአብሔር ነውና።**

# ስለ እምነት

- ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ፥ ስለዚህም **የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን**። (ዕብ. 11፥3)
- **ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም**፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና ። (ዕብ. 11፥6)
- 13 ነገር ግን። አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ ተብሎ እንደ ተጻፈ ያው አንዱ **የእምነት መንፈስ** ስላለን፥ እኛ ደግሞ እናምናለን ስለዚህም እንናገራለን፤ (2ኛ ቆሮ. 4፥13)
- **የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት**፥ **ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን** የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው። (2ኛ ቆሮ. 4፥17-18)

# ማሳሰቢያ

በተለያየ መንገድ በዚህ ሕንጻ ማፈላለጉ ሥራ ልትተባበሩን ፈቃደኛ የሆናችሁ ወንድሞችና እህቶች እርዳታችሁንና ድጋፋችሁን እጅግ አድርገን እንፈልጋለንና - ይህ ስራ የሁላችን ነው::

- የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን (መሪዎችን)/በፕሮጀክት ቡድኑ ውስጥ ያለነውንም እንድታነጋግሩ በጌታ ፍቅርና ትህትና እንጠይቃለን::
- ጌታ ይባራካችሁ!